# ለታናሽ ወንድሜ
# ለአርበኛ ተከተል
(ከደቅሲሶ ከተቦ)

ይድረስ ካለህበት ለታናሽ ወንድሜ
ለጤናህ እንዴት ነህ አየሁህ በህልሜ፡
እኔ እንዳለሁ አለሁ ህማምን ታምሜ
የናት ሞት እያየሁ ተገትሬ ቆሜ።

ሀኪም አያውቅልኝ ወይ አልሞት ወይ አልድን፡
በቁሜ ፈዝዤ እንዲሁ እንደ በድን።
ብበላ አይጠጋኝ ቢቀቡኝ አልወዛ፡
ጨዋታ አያምርብኝ ቀልዴ የለው ለዛ።
መሸ ጠባ እህህ እንደ ቋያ ነዶ፡
አልቅሽ አይወጣልኝ የናትአለም መርዶ።

ዝንተአለም እሮሮ
ይህም ተብሎ ኑሮ:
የጨለማው ጽልመት የቅጥቃጤው መንጋ፡
ሲያባትተኝ ያድራል አልብሎኝ አልነጋ።
ወንድምአለም ከንዴ
ከቶ ትዝ ይልሃል ያለችን እናቴ፡
አንተነን ተከተል እኔን ደግሞ ምራው በታላቅነቴ።

ቃሏንም ጠብቀን አንተ ብትከተል እኔ ፊት ብመራ
ማን ያጠቃን ነበር እንኩንስ ኩታራ፡
ግና ምን ያደርጋል
ምራ የተባልኩት ሆንኩብህ ደንባራ።
እንግዲህ ያውልህ ውሰድ ብኩርና፡
መዋደቅ መምራቱ ባንተ ያምራልና።
ሂድ እንግዲህ ግጠም ጃሎ በል አርበኛው፡
ለደም ደም ነውና ስርየት መዳኛው።

ሚያዝያ 2001